## መግቢያ

የዮሐንስ መልዕክት እንደ ሌሎች መልዕክቶች ለአንድ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ አይደለም። ዳግም ልደትን አግኝተው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ላላቸው ሁሉ የተጻፈ መልዕክት ነው።

እግዚአብሔር ብርሃን፥ ጽድቅና ፍቅር ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች በብርሃን የሚመላለሱ፥ በጽድቅ የሚራመዱ፥ በፍቅራቸው የሚታወቁ፤ በአጠቃላይ በዕለት ኑሯቸው የአባታቸውን ባህርይ የሚያሳዩ ናቸው።

ስለ ክርስቶስ ያለን እውቀትና ትምህርት ሙሉ መሆን አለበት። ስለክርስቶስ ያለን እውቀትና ትምህርት ሙሉ የሚሆነው፤ ከሰማይ ወርዶ ሥጋን እንደለበሰ፥ በዚህም ሥጋ ለባሽ የሚኖረውን ኑሮ እንደኖረ እና ሥጋ እንደመልበሱ ሞትን በሥጋው እንደቀመሰ ስንቀበል መሆኑን ይገልጻል። ከዚህ ያነሰ ማንኛውም ትምህርትና መርዳት ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባና ሀሰተኛ መሆኑን ዮሐንስ ያስተምራል።

## <u>የመልዕክቱ ጽሀፊና ተቀባዮች</u>

እንደ ዮሐንስ ወንጌል በዮሐንስ መልዕክትም ስለጸሐፊው ግልጽ የሆነ ነገርን አናገኝም። ሆኖም ራሱን የሚገለጽባቸው አባባሎች አሉት። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ዮሐንስ ራሱን "ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀመዝሙር" (ዮሐ. 13፡23, 21፡20) በማለት ይገልጻል። ስሙን ሳይጠቅስ በአንድ ወቅት በተወሰነ ሥፍራ የነበረ ምስክር መሆኑን የሚገልጽበትም አገላለጥ አለው። (ዮሐ. 21፡24)

ዮሐንስ በመጀመሪያ መልዕክቱ የሚጽፍላቸውን "ልጆቼ" እና "ወዳጆች" እያለ በመጥራት ያለውን የጠበቀ ኅብረት ይገልጣል። በመጀመሪያ መልዕክቱም ሆነ በሌሎቹም እንደዚህ ዓይነት አባባሎችን ይጠቀማል እንጂ ራሱን በስም አይገልጥም። በ2ኛ እና 3ኛ መልዕክቱ ዮሐንስ ራሱን "ሽማግሌው" በማለት ይጠራል።

በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ዘንድ ራሱን በስሙ ባለመጥቀስ የታወቀ ስለሆነ እና በሌሎች የጥናት መረጃዎች መሠረት ሦስቱን መልዕክቶች ሐዋሪያው ዮሐንስ እንደጻፋቸው ይታመናል።

## <u>መልዕክቱ ከሌሎች መጽሐፍት ጋር</u>

የዮሐንስ መልዕክት በሚሰጠው መክፈቻ ሀሳብ ከዮሐንስ ወንጌልና ከራዕይ መጽሐፍ ጋር ተመሳሳይ ነገር አለው። ስለዚህም እነዚህን መጽሐፍት ሐዋሪያው ዮሐንስ እንደጻፋቸው ይታመናል።

አንደኛ ዮሐንስ መልዕክት መሠረታዊ የክርስትና እምነትን አስመልክቶ ስለ አብ፥ ስለ ወልድ እና ስለ አማኞች የሕይወት ጥራት የሚያስተምር መጽሐፍ ነው።

አብ ለሰው ልጆች መዳን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደላከው እና ልጁም ለኃጢአታቸው እንደሞተ ያስተምራል። (1ዮሐ. 2፡2,4፡9-10, 14) በዚህም የዮሐንስ መልዕክቶቹ ከወንጌላትና ከጳውሎስ መልዕክቶች ጋር ይመሳሰላል። (ማቴ. 11፡25-27, ሉቃስ 10፡21-22 ሐዋ 3፡19 ሮሜ 3፡25, 8፡15-17 ገላ. 4፡4 ኤፌ 2፡1-10 ዕብ 4፡15- 5፡10, 9፡10 9፡11-10፡18)

በመልዕክቶቹ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለመፈጸም፥ ሐሰተኛ መንፈስን ስለመለየት፥ በጽድቅ ስለመመላለስና ባልንጀራን እንደራስ ስለመውደድ በስፋት ተጽፉል። ይህም ደግሞ ከሌሎች መጻሐፍት ጋር እንዲመሳሰል ያደርገዋል።

የዮሐንስ መልዕክቶች ባዘሉት ትምህርት ከሌሎች መጽሐፍት ጋር ቢመሳሰሉም፤ የሚለዩበትም ነገር አለ። መልዕክቶቹም እንደ ሌሎች መልዕክቶች በሰላምታ ጀምረው በቡራኬ አይጨርሱም። በዚህ ለየት ያሉ ናቸው። (የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት 1ጴጥ፡1፡1-2፤ 5፡14)

## የመልዕክቶች አበይት ሀሳቦች

የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑና እውነትን ለመጨበጥ ለሚሹ ዮሐንስ በመልዕክቶቹ የሚከተሉትን ቁልፍ መንፈሳዊ እውነቶችን አስፍሮል።

1. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ሥጋን ለብሶ መመላለሱ አፈታሪክ አይደለም። የታየ፥ የተደመጠና የተዳሰሰ ጌታ ነው። (1ዮሐ 1፥1-2) ስለጌታ የምንመሰክረው ስለአየነውና ስለቀመስነው ነው።
2. የእግዚአብሔር ልጆች የአባታቸውን ባህርይ የሚገልጹ ናቸው። እግዚአብሔር ታማኝ፥ ጻድቅ፥ በጐና ንጹህ ነው። ልጆቹም በታማኝነት፥ በጽድቅ፥ በበጎነት እና ያለነቀፋ መመላለስ ይጠበቅባቸዋል። (1ዮሐ. 1፥5, 7, 9, 2፥12 3፥3, 7 4፥7-12, 16, 19 5፥20 3ዮሐ. 11)
3. በመጨረሻው ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ ስለሚነሳ ገጽታውን ለይተህ እወቅ። ክርስቶስ በሥጋ እንደተገለጠ የማይቀበል ያ ሐሰተኛ ነው። (1ዮሐ. 2፥18, 22, 28, 3፥2-3, 4፥3, 17-18 2ዮሐ. 7,8)
4. የክርስቶስ ማንነት በሥጋ ከመገለጡ ጋር የተያያዘ ነው። እርሱ ከሰማይ የወረደ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። (1ዮሐ.2፥22-23, 4፥2, 15, 5፥1, 5, 10,20 2ዮሐ. 7-10)
5. ክርስቶስ በሥጋው ያከናወነው የድህንነታችን ዋስትና ነው። (1ዮሐ. 1፥7-9, 2፥2, 12, 3፥5, 4፥10) /ዘሌ 4፥1-35, 16፥1-34, 1ጴጥ. 1፥18-19/
6. በክርስቶስ በማመን የሚገኘው ዘላለማዊ ሕይወት ጽኑ ምስክር አለው። 1ዮሐ. 5፥9-12
7. የእግዚአብሔር ልጆች መለያቸው በፍቅርና በእውነት መመላለሳቸው ነው። (1ዮሐ. 1፥6-7 2፥3-6, 9-11, 3፥6-18, 24, 4፥7-12, 20-21፤ 2ኛዮሐ. 5-7፤ 3ኛ ዮሐ. 7)

## ጥናት አንድ

## “በእርሱ መኖር”

**1ዮሐ. 1፥1-10, 2፥1-6**

መግቢያ፡- በዚህ ጥናት ዮሐንስ በመጀመሪያ ስለነበረና በዓይን ስለታየ፥ በእጅ ስለታደሰሰ፥ ስለተሰማ ታላቅ ጌታና ከእርሱ ጋር ኅብረት በማድረግ ስለተገኘ ሕይወት የጻፈውን እንመለከታለን።

ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለንን ኅብረት በብርሃን የመመላለስ ሕይወት እንደሆነም ይገልጻል። በኃጢአት (በጨለማ) ያሉን ነጻ ያወጣ ዘንድ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ስላለው የማንጻት ኃይልም የጻፈውን እናጠናለን።

ዓላማ፡- ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አለን ካልን በብርሃን መመላለስ ምርጫ ሳይሆን ሕይወታችን፥ ማንነታችን መሆኑን ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቁጥር 1ን በመመልከት
   - ሀ. ስለሕይወት ቃል የሚናገራቸው አራት ፍሬ አሳቦች ምን ምን ናቸው?
   - ለ. ስለማን ነው ይህን የሚናገረው?
   - ሐ. ይህ አገላለጽ ምን ያመለክታል?
2. በቁጥር 2 - 4 እንደተጻፈው
   - “ሕይወትም ተገለጠ” ሲል ስለማን ነው የሚናገረው?
   - ስለተገለጠው ሕይወት ምን ይላል?
   - ኅብረታችን ከማን ጋር ነው?
   - እንዴት? ምንስ ማለት ነው?

3. በቁጥር 5 - 6 *መሠረት*
    - ከእርሱ የሰሙት ምንድን ነው?
    - ኅብረት እንዳለን በምን ይገለጻል?
    - ውሸታም የሚያሰኘን ምክንያት ምንድን ነው?
    - ምንን ለመግለጽ ነው ብርሃንና ጨለማን የተጠቀመው?

4. ከቁጥር 7 - 10 እንደተገለጸው
    - ከኃጢአት ለመንጻት የቅዱሳኑ ድርሻ ምንድን ነው?
    - ኃጢአት አልሠራንም ወይንም የለብንም ብንል በምንባቡ *መሠረት* ምን ማለታችን ነው?
    - በምን እንመለስ ይላል?
    - ስለክርስቶስ ኢየሱስ ደም ኃይልና *ሥራ* ምን ተጠቅሷል?
5. በ1ዮሐ. 2፣1 - 2 *መሠረት*
    - ኃጢያትን አስመልክቶ የሚሰጠው ትዕዛዝና ምክር ምንድን ነው?
    - “አለን” ስለሚለው ጠበቃ ማንነት የተዘረዘረው ምንድን ነው?

        ለመሪው፡- ከአብ ዘንድ የተሰጠ፤ ጻድቅ የሆነ፤ ስሙም ኢየሱስ ነው።
    - ከጠበቃነቱ ባሻገር ስለሥራው የተገለጸው ምንድን ነው?
    - ለነማን ነው ይህን የሚያደርገው?
6. ቁጥር 3-4 ላይ እንደተዘገበው
    - ጌታን ማወቃችን የሚገለጠው በምንድን ነው?
    - ይህ የማይታይበት እንዴት ነው የተገለጠው?
    - ምንስ ማለት ነው?
7. በቁጥር 5-6
    - ቃሉን በሚጠብቅ ምንድን ነው ተፈጽሟል ያለው? ይህን እንዴት ትረዳዋለህ?
    - በእርሱ ያለ ሰው ምን ይጠበቅበታል?
    - በእርሱ እንዳለን በምን ይታወቃል?

## ማዛመድ

1. በዚህ ክፍል ስለ ኃጢአት የተገነዘብከው *መሠረታዊ* እውነት ምንድን ነው?
2. እግዚአብሔርን ስናውቅና የማወቃችን መግለጫ መንገድ ምን እንደሆነ ተገነዘብክ?
3. በእግዚአብሔር እኖራለሁ ስንል ሁልጊዜ ልናስተውልና ልንከተለው ስለሚገባን ምሳሌ የተገነዘብከው ምንድን ነው?

የሚጠና ጥቅስ 1ዮሐ. 1፣7-10

## ጥናት ሁለት

## “በብርሃን መኖር”
**1ዮሐ. 2፥7-29**

*መግቢያ፥-* ዮሐንስ በዚህ ክፍል በብርሃን አለን የሚሉ በዓለም ያለውን መውደድ እንደሌለባቸውና በብርሃን ሊመላለሱ እንደሚገባ ያሳሰበውን እንመለከታለን። በተጨማሪም ከሐሰተኛ አስተማሪዎች እንድንጠበቅ የሰጠውን ምክር እናጠናለን።

*ዓላማ፥-* በእግዚአብሔር ፍቅር የሚኖር ዓለምንና በዓለም ያለውን ነገር የሚጠላና ወንድሙን የሚወድ ልብ እንዳለው ለማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቁጥር7-8
   - ዮሐንስ ስለሚጽፍላቸው ትዕዛዝ የተገለጸው ምንድን ነው?

     *ለመሪው፥-* ከመጀመሪያ የነበረች፤ ቀድሞ የተሰማች፤ ያልተለወጠች።
   - በእርሱና በእናንተ እውነተኛ ነው የሚለው ስለምንድን ነው? ምንን ለመግለጽ ነው?
   - በመቀጠል ጨለማና ብርሃንን አስመልክቶ የሚናገረው ምንድን ነው?
   - ስለትዕዛዝ ከሚናገረው ጋር ይህስ እንዴት ነው የሚያያዘው?
2. ቁጥር 9-11
   - በብርሃን ሆነ በጨለማ የሚመላለስ ሰው የሚታወቀው በምንድን ነው?
   - በጨለማ አለ ስለሚለው ሰው የሚናገራቸው ሁለት ሀሳቦች ምን ምን ናቸው? ምንስ ያመለክታሉ?
3. ከቁጥር12-14 *መሠረት*
   - ልጆችን አባቶችንና ጐበዞችን አስመልክቶ የተጻፈው ምንድን ነው?

     *ለመሪው፥-*

     ልጆች፥ ኃጢአታቸው ተሰርዮላቸዋል፤ አብን ያውቃሉ

     አባቶች፥ በመጀመሪያ የነበረውን ያውቃሉ።

     ጐበዞች፥ ክፉውን አሸንፈዋል፤ ብርቱ ሆነዋል፤ የእግዚአብሔር ቃል በውስጣቸው አለ።
   - የሚጽፍላቸው ሀሳብ ከማንነታቸው ጋር እንዴት ነው የሚያያዘው? ምንስ ያመለክታል?
4. ከቁጥር15-16 *መሠረት*
   - አትውደዱ የሚለው ምንድን ነው?
   - ዓለምና በዓለም ያሉትን ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - በዓለም ያሉ ምንድን ናቸው?
   - እነዚህ ነገሮች ከዘፍ 3፥6 ጋር ምን መመሳሰል አለው?
   - በአለም ያለውን የሚወድ በውስጡ ምን የለም? ምን ማለት ነው
5. በቁጥር 17 ያልፋልና ይኖራል በማለት የሚገልጸው ምንድን ነው? ምንስ ያመለክትሃል?
6. በቁጥር 18 *መሠረት* የመጨረሻውን ዘመን የሚያውቁት እንዴት ነው?

   *ለመሪው፥-* የክርስቶስ ተቃዋሚ መምጣቱና መነሳቱ።
7. በቁጥር19 ከነሱ ዘንድ የወጡትና ያልጸኑት እነማን ናቸው? ለምን?
8. ከቁጥር 20-21 *መሠረት*
   - የተቀበሉትና የሚያውቁት ምንድን ነው?
   - ሁሉን ታውቃላችሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - ምን ስላላቸው ነው የሚጽፍላቸው?
9. ቁጥር 22-25ን በመመልከት
   - ስለመካድና መታመን የተገለጸው ምንድን ነው? (ቁጥር 22-23)

- በቁጥር 24-25 ይኑር፥ ቢኖር እና ትኖራላችሁ በማለት የሚያሳስባቸው ሀሳብ ላይ ተወያዩበት። ተስፋቸውስ ምንድን ነው?

10. በቁጥር 28-29 ስለመጨረሻው ጊዜና ስለጽድቅ ምንድን ያስገነዝባቸዋል?

*ለመሪው፡-*

- ጌታ በሚገለጥበት ወቅት በእርሱ መሆን
  - በእምነት (በድፍረት) ያቆመናል።
  - ከእፍረት ይጠብቀናል።
- ከእርሱ የተወለደ ጽድቅን ያደርጋል። (1፡5, 2፡1,20 3፡7 ን ተመልከት)
  - እሱን ስናውቀው በምግባራችን እሱን እንመስለዋለን።
  - ተግባራችን ማንነታችንን (ትውልዳችንን) ያሳያል።

## ማዛመድ

1. ከዛሬው ጥናት የእግዚአብሔር ፍቅር በአንተ መኖሩን ስለምትገልጥበት መንገድ ምን ተገንዘብክ። ለምንስ እርምጃ ተዘጋጅተሃል?
2. በብርሃን ስለመመላለስ የተረዳኸውን ለቡድንህ አካፍል።
3. ዓለምንና በዓለም ያሉትን መውደድን አስመልክቶ የተማርከውን ለሌሎች አካፍል።

# ጥናት ሦስት

# "የጌታ ልጆች ባህርይ"

## ዮሐ. 3፡1-24

**መግቢያ፡-** የጌታ ልጆች በእግዚአብሔር ፍቅር የተጀመረ ሕይወት አላቸው። ይህ ሕይወት ደግሞ ሌሎችን የሚወድና ኃጢአትን የሚጠላ ዘር በውስጡ አለው። ስለዚህ በዛሬው ጥናታችን የእግዚአብሔር ልጆች ስላላቸው መዋደድና በአብ ዘንድ ስላላቸው ድፍረት እናጠናለን።

**ዓላማ፡-** ዳግም የተወለደ ሰው ከኃጢአት የሚርቅ፤ ወገኖቹን የሚወድና ራሱን ለአብ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑን ለማስገንዘብ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር1-2 ን በመመልከት
   - እዩ (ተመልከቱ) የሚላቸው ምንድን ነው?
   - ስለእግዚአብሔር አብ፥ ስለ አማኞች እና ስለ ዓለም የተጠቀሰው ምንድን ነው?
   - እርሱን እንድንመስል እናውቃለን ሲል ምን ማለት ነው?
2. በቁጥር 3 ተስፋ የሚደረገው ምንድን ነው? በማን? ተስፋ አደራጊውስ ያለበት ኃላፊነት ምንድን ነው?
3. ከቁጥር 4-6
   - ኃጢአት ምንድን ነው?
   - በቁጥር 5 "እርሱ" የሚለው ማንን ነው?
   - እንዴት ነው ከኃጢአት ጋር ያነጻጸረው?
   - ከቁጥር 1-6 በመደጋገም የተጠቀሰው ምንድን ነው?
   - በቁጥር 3 እና 7 ላይ ስለ እርሱና ስለ ልጆቹ የተጠቀሰውን በዝርዝር ተወያዩበት።

ለመሪው፡- ሁሉ ከእርሱ ጋር መያያዙን ልብ በል
ንጹህ፡- ብንሆን እንደርሱ
ጽድቅ፡- ብንሠራ እንደርሱ

- ኃጢአት የሚያደርግና የማያደርግ ከማን ነው?

4. በቁጥር 8
   - ኃጢአትን የሚያደርግ ከማን ነው?
   - ክርስቶስ የተገለጠው ለምንድን ነው?
   - ምን ማለትስ ነው?
5. ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን ሊያደርግ እንደማይችል የተሰጠው ምክንያት ምንድን ነው?
   ከ 1ዮሐስ. 1፡9 ጋር እንዴት ታስተያየዋለህ?
6. በቁጥር 10 የተጠቀሱ የሁለት ልጆች ልዩነት ምንድን ነው? የሰው ማንነቱ በምኑ ነው የሚገለጠው? (ከ3፡9-11 ሀሳብ ጋር በማስተያየት ተመልከቱ)
7. በቁጥር 11-12 ቃየል አቤልን የገደለበት ምክንያት ምንድን ነው?
   ለመሪው፡- የ2፡9-11 ሀሳብን ተመልከት
8. ቁጥር 13 ከ11-12 ካለው አሳብ ጋር ምን ያገናኘዋል? (ለመሪው፡- አትደነቁ የሚለውን ሀሳብ ልብ በሉት)
9. በቁጥር 14-15 ወንድምን በመውደድና አለመውደድ መሐል የተገለጸው ልዩነት ምንድን ነው?
10. በቁጥር 16
    - “እርሱ” የሚለው ማንን ነው? ምን አደረገልን?
    - ከእርሱ ስለምን ተረዳን? ለምንስ ዓይነት ተግባራዊ ምላሽ ያነሳሳናል?
    - የተሰጠን ምሳሌ ያደረገውና ከእኛ የሚጠበቅብን ምንድ ነው?
11. በቁጥር 17-18 መሠረት ፍቅራችንን ለወንድማችን እንዴት ነው የምንገልጸው?
    ለመሪው፡- ፍቅር የቃላት ጋጋታ ሳይሆን ልብ በሚደርስ ተግባር የሚገለጽ ነው። (ያዕ. 2፡15, 1ቆሮ. 13፡1)
12. በቁጥር 19-21 መሰረት
    - ከእውነት እንደሆንን እንዴት እናውቃለን?
    - ይህስ እንዴት ነው የሚመዘነው? (20-21)

    ለመሪው፡- በ1፡3,6 ስለ ኅብረት የተገለጸውን ልብ በል።
13. ከቁጥር 22-24 በመመልከት
    - የለመንነውን እንድንቀበል ድፍረት የሚሆኑን ፍሬ አሳቦች ምን ምን ናቸው? (ቁጥር 22)

      ለመሪው፡-
      - ትዕዛዙን መጠበቅ
      - ደስ የሚያሰኘውን ማድረግ (ዮሐ 8፡28-29, 11፡42, 16፡20-27)
    - ትዕዛዚቱ ምንድን ነች? (23)
    - ትዕዛዚቱና አብን ደስ የሚያሰኝ ነገር ምንድን ነው? (ማመንና መዋደድ)
    - ትዕዛዙን የሚጠብቅ የተሰጠው ተስፋ ምንድን ነው?
    - ይህስ እንዴት ይታወቃል?

## ማዛመድ

1. በዚህ ጥናት ኃጢአትን የሚያደርጉና የማያደርጉ የተሰጣቸውን የኅብረት ልዩነት ልብ በል። ይህ ስለ ኃጢአት ያለህን አመለካከት እንዴት ይቀይረዋል?
2. ወንድምህን መወደድ እስከምን ድረስ ነው? ይህ በህይውትህ እንዴት ይገለጣል?
3. ከእውነት መሆንህን እንዴት ታውቃለህ? ይህ በዕለት ኑሮህ ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?
4. ልመናህ የመመለሱ እርግጠኛነትን አስመልክቶ ምን ተማርክ? ይህ ስለ ጸሎትህ ምን ያስገንዝባል?

   ለመሪው፡-
   ትዕዛዙን በሚጠብቅና አብን ደስ በሚያሰኘው ሂደት ውስጥ መገኘት። ጽሎት ከሕይወት ጋር ሲሆን ኃይል አለው።

## ጥናት አራት

## “በፍቅር ያለ በእርሱ አለ”
### ዮሐ. 4፥1-21

**መግቢያ፥-** በዛሬው ጥናታችን ዮሐንስ ከጌታ የሆነን መንፈስ ስለምንለይበት መንገድ እና ስለ ፍቅር የጻፈውን እናጠናለን። ዮሐንስ ክርስቶስ በሥጋ መገለጡን የማይቀበል ሐሰተኛና የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ መሆኑን ያስተምራል። ፍቅርን በተመለከተ ደግሞ እንዴትና ለምን መዋደድ እንዳለብን የጻፈውን ድንቅ እውነት እንመለከታለን።

**ዓላማ፥-** በጌታ እንዳለንና እርሱን ማወቃችን በምናሳየው ፍቅር የሚገለጥ መሆኑን ለማስገንዘብ።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 1-3 በመመልከት
   - አትመኑና መርምሩ የሚላቸው ስለምንድን ነው? ለምን?
   - የእግዚአብሔርን መንፈስ የሚለዩት በምንድን ነው?
   - በሥጋ መምጣቱን ማመን አስፈላጊነቱን ተወያዩበት።
     ለመሪው፥- በሥጋ መምጣቱን መካድ በሚከተሉት ጥቅሶች ላይ ባሉ እውነቶች ላይ ያለውን ተጽዕኖ ልብ በል። 1ዮሐ. 1፥7-8, 2፥1-2, 3፥8 5፥10-12,20-21
2. በቁጥር 4 ዮሐንስ ቅዱሳንን እንዴት ነው የሚያበረታታቸው? ለምን?
3. በቁጥር 5-6 የእውነትና የስህተትን መንፈስ ለመለየት በማነጻጸር የሚሰጠው መመዘኛዎች ምንድን ናቸው?
4. በቁጥር 7-8 ስለፍቅር የሚናገራቸው ነጥቦች ምን ምን ናቸው?
   ለመሪው፥-
   - ፍቅር ከእግዚአብሔር ነው፤ እራሱም ፍቅር ነው።
   - ከጌታ የተወለደ ሌሎችን ያፈቅራል
   - ፍቅር ያለው ጌታን ያውቃል/ ጌታን ስለምናውቅ እንዋደዳለን።
5. በቁጥር 9-11 የእግዚአብሔር ፍቅር በማንና እንዴት ተገለጠ? ከምን የተነሳና ለምን ዓላማ ተገለጠ? ከእኛስ የሚጠበቅብን ኃላፊነት ምንድን ነው? (11)
6. በቁጥር 12
   - እግዚአብሔርን ስለማየትና በእኛ ውስጥ ስለመኖሩ የተጠቀሰውን ሀሳብ ተወያዩበት።
   - የተሰጠን ተስፋ ምንድን ነው?
   - ፍቅሩ ፍጹም ይሆናል ሲል ምን ማለት ነው?
7. በቁጥር 13 እኛ በእርሱ እርሱም በኛ መኖሩን እንዴት እናውቃለን? (ለመሪው፥- በመንፈሱ እና ፍቅሩ በኛ ሲታይ)
8. ከቁጥር 14-15 ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት እንዴት አድርጐ ነው የተገለጠው?
   ለመሪው፥-
   - የታየና የተመሰከረ ነው (አባት ልጁን አዳኝ አድርጎ እንደላከው)
   - የኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅነት ማመን
9. በቁጥር 16 ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?
   ለመሪው፥-
   - ፍቅር ራሱ ጌታ መሆኑን
   - ፍቅር የሚታወቅ ነው
   - ፍቅር የሚታመን ነው
   - ፍቅር የሚኖርበት ነው
   - ፍቅር ኅብረትን ያሳያል
10. በቁጥር 17-18 ስለ ፍርድና ፍርሃት የገለጸው ምንድን ነው?
    - “ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን ይጥላል” ሲል ምን ማለት ነው?
    - ስለ የትኛው ፍርሃት ነው የሚናገረው?

11. በቁጥር 19-21 ሰውን ሐሰተኛው የሚያደርገው ምንድን ነው? አንድን ሰው ለመውደድ መሠረቱ ምንድን ነው? (ቁጥር 19)

### ማዛመድ

1. ከዛሬው ጥናት ከጌታ ያልሆነን መንፈስ ስለምንለይባቸው ሁለት እውነቶች የተረዳኸውን ለቡድንህ አካፍል።
2. ሌሎችን መውደድህ እግዚአብሔርን ማወቅህ መሆኑን መረዳትህ ምን ይጠቅምሃል?
3. መዋደድ ስንል በቁጥር 10-11 መሠረት ምን ማለታችን ነው? ፍቅርህ እስከ ምን ድረስ ነው?
4. እግዚአብሔርን ማወቅና ማመን ከፍቅር ጋር እንዴት እንደሚያያዝ የተረዳኸውን አስረዳ። ይህ በዕለት ኑሮህ ለምን ያነሳሳሃል?

## ጥናት አምስት

## "ምስክር"

### ዮሐ. 5፥1-21

መግቢያ፡- በዛሬው ጥናት ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የተወለደ በእምነቱ አለምን እንዳሸነፈ ያስተምረናል። በተጨማሪ በወልድ የሚያምን በህይወቱ እንደ ማኅተም የሚሆን ምስክር እንዳለው ሐዋሪያው በማስረገጥ ያሰፈረውን እውነት እንመለከታለን።

ዓላማ፡- አማኝ በእምነቱ አለምን የሚያሸንፍ፥ በፍቅሩ ጌታውን የሚመስል እና የዘላለም ህይወት እንዳለው ጽኑ ምስክር ያለው መሆኑን ማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር 1-2 መሠረት
   - በኢየሱስ የሚያምን ምን ይሆናል?
   - ወላጁን የሚወድ ምን ይጠበቅበታል?
   - እግዚአብሔርን እንወዳለን እንታዘዛለን ማለት የምንችለው መቼ ነው?
2. ቁጥር 3-5 በመመልከት
   - ለምንድን ነው ትዕዛዙ ከባድ አይደለም ያለው?
   - ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው?
   - እንዴት ነው ዓለምን የምናሸንፈው?
3. ዮሐንስ በቁጥር 6-8 ስለምንድን ነው የሚናገረው?

   ለመሪው፡-

   በነዚህ ቁጥሮች ላይ በርከት ያሉ አተረጓጓሞች አሉ። ዮሐንስ በምዕራፍ 4 እውነተኛና ሐሰተኛን መንፈስ መለየው ክርስቶስ በሥጋ መምጣቱን ከመቀበል ጋር መያያዙን ይናገራል። በምዕራፍ 5 ደግሞ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን (በ5፥5, 6, 20) እና ወደ ምድር ወርዶ ሥጋን መልበሱን ይናገራል።

"በውኃና በደም የመጣ" የሚለውን ሀረግ መሰረታው ሀሳብ፥ ሙሉ ለሙሉ ይህን ነው የሚያመለክተው ማለቱ ትንሽ ያስቸግር ይሆናል። ቢሆንም ለሥጋ ለባሽ እንግዳ ያልሆነን "ውኃና ደምን" በማንሳት ጌታ ሥጋለበሰ እንደነበር ለማሳየት ሞክሯል። በውኃና ደም የመጣ ሲል፥ በውኃ በመጠመቁ የንስሃ ፍሬን ማሳየቱን፤ በደሙ ዓላማ ያለውን ሞት መሞቱን ያሳያል በማለት አንዳንዶች ያስተምራሉ። በዮሐንስ ወንጌል 19፡34 ካለው ሀሳብ ጋር የሚያይዙትም አሉ። እነዚህ ደግሞ ጌታ ራሱን ለሰው ልጆች አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ከጐኑ የፈሰሰውን ውኃና ደምን ያመለክታል በማለት ስብእናውን የሚያመለክት የአገላለጽ ዘይቤ አድርገው ይወስዱታል። በአጠቃላይ የአተረጓጎም ልዩነቶች ቢኖሩም የሁሉም መረዳት የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅን ለማዳን ሥጋ እንደለበሰ ነው።

4. በቁጥር 9-12
   - ስለ ልጁ የመሰከረው ማነው?
   - ከማመንና ካለማመን ጋር እያያዘ የሚገልጣቸው እውነቶችን በዝርዝር ተመልከታቸው።

   ለመሪው፡-
   - ማመን፡-
     - ያመነ በነፍሱ ምስክር አለ (መንፈስ
     - የእግዚአብሔር ልጅን በማመን የዘላለም ሕይወት አለ
   - አለማመን
     - የተገለጠውን ምስክር መካድ ነው
     - አብን (የላከውን) ሐሰተኛ ማድረግ ነው
     - ሕይወትን ማጣት ነው
5. በቁጥር 13-15 በመመልከት
   - ዮሐንስ መልዕክቱን የጻፈው ለነማን እና በምን አላማ ነው?
   - መልዕክተቶቹን የሚጽፍላቸው ስለአላቸው ድፍረትና ስለ ጸሎታቸው የሚያስተልልፈው መልዕክት ምንድን ነው?
6. በቁጥር 16-17 መሠረት
   - ሐዋሪያው ስለምንድን ነው የሚናገረው?
   - ሞት የሚገባውና የማይገባው ኃጢአት ሲል ምን ማለት ነው?
   - ከ1ዮሐ. 1፡9-10 ጋር እንዴት የሚስማማ ይመስልሃል?
7. በቁጥር 18-21
   - በቁጥር 18 ከእግዚአብሔር የተወለደን አስመልክቶ እናውቃለን በማለት የሚዘረዝራቸው ምንምን ናቸው? እንዴትስ ይያያዛሉ? እንዴትስ ትረዳቸዋለህ?

     <u>ለመሪው፡-</u>
     - ኃጢአትን አያደርግም
     - ራሱን ይጠብቃል
     - ክፉም አይነካውም
   - ከቁጥር 19-20 እናውቃለን ብሎ የሚዘረዝራቸው ሀሳቦች ምንምን ናቸው? እንዴት ትረዳቸዋለህ?

     ለመሪው፡-
     - እኛ ከእግዚአብሔር እንደሆንን
     - ዓለም በክፉ መያዙን
     - የእግዚአብሔር ልጅን መምጣት
     - እውነተኛውን ለማወቅ ልቦና እንዳለን
   - በማን አለን ይላል? ይህስ ማን ነው?
8. በቁጥር 21 ከምን እንዲርቁ ነው የሚመክራቸው? ከመጽሐፉ አጠቃላይ ሀሳብ አንጻር ምን ማለቱ ነው? ለእኛስ ምን ይሆን?

## ማዛመድ

1. ከዛሬው ጥናት ዓለምን ልታሸንፍ ስለምትችልበት መንገድ ምን ተማርክ? (በምንና እንዴት ነው)
2. በዮሐንስ መልዕክት ተደጋግሞ እግዚአብሔርን መውደድ ልጆቹን መውደድ እንደሆነ ተመልክተናል።
   ሀ. መጥላት ምርጫ አለመሆኑን መገንዘብ
   ለ. ሌሎችን መውደድ እግዚአብሔርን መውደድ መሆኑን መረዳት።
   ወደ ፊት ለምትኖረው ኑሮ ምን ያስገነዝብሃል?
3. እግዚአብሔርን ስንጠይቅ ልብ ልንላቸው የሚገቡን መሠረታዊ መመሪያዎች ምንድን ናቸው? (ቁ.14-15)

## ጥናት ስድስት

## “እውነተኛ ሁን”

**2ዮሐ. 1፥1-13**

*መግቢያ፡-* በዛሬው ጥናታችን ዮሐንስ እመቤት ብሎ ለሚጠራት ልጆችሽ የሚላቸውን በእውነት ሲመላለሱ በማግኘቱ እንዴት ደስ እንደተሰኘ በመግለጽ የጻፈውን አጭር ደብዳቤን እንመለከታለን። በመልዕክተም እርስ በርስ ስለመዋደድና ከአሳቾች እንዲጠበቁ ምክርን ይሰጣል።

*ዓላማ፡-* ፍቅራችንም ሆነ አረማመዳችን ሁሉ እውነተኛ ሊሆኑ እንደሚገባ ለመገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር 1-2 ስለሴትየዋና ስለልጆችዋ የተገለጠው ምንድን ነው?
2. በቁጥር 3 በሰላምታው የሚያስተላልፈው በረከት ምንድን ነው? ምንጩ ማነው? በምን ሁኔታ ከነሱ ጋር ይሆናሉ?
   *ለመሪው፡-*
   - ጸጋ፥ ምህረት፥ ሰላም
   - ምንጩ አብና ወልድ
   - ከነሱ ጋር የሚሆነው በእውነትና በፍቅር ነው።
3. በቁጥር 4 የተደሰተበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. በቁጥር 5-6 እለምንሻለሁ እና ትዕዛዝም ነው በማለት የሚናገራት ለምንድን ነው?
5. በቁጥር 7-8 ስለ አሳቾች የተዘረዘረው ምንድን ነው? ለሚጽፍላቸው የሚስጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? ምንስ ማለቱ ነው? (1ዮሐ. 2፥18,28, 3፥2 ማቴ.5፥12 ዮሐ. 4፥36, 1ቆሮ. 3፥8 ራዕይ 11፥18, 22፥12)
6. ከቁጥር 9-11 መሠረት
   - አብና ወልድ የሌሉትን ሰው እንዴት ነው የገለጠው?
   - ከእንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር ሊኖር ስለሚገባ ግንኙነት የተሰጠው ምክር ምንድን ነው?
   - ምን ማለት ነው? እንዴት ትረዳዋለህ?
7. በቁጥር 12-13 ጸሐፊው መልዕክቱን የሚጠቀልልበትን ሦስት አንኳር እውነታዎች ዘርዝር።
   *ለመሪው፡-*
   - ሊጽፈው ያለው ብዙ መሆኑ
   - ፊትለፊት ሊያያቸው መናፈቁን
   - ከሌሎች ስላምታ ማቅረቡ

### ማዛመድ

1. የምትገልጸው ፍቅር በእውነት ሊሆን እንደሚገባ ምን ተገነዘብክ?
2. የምታደርገውና የምትናገረው በእውነት ላይ የተመሠረተ ነውን? ምንስ ማድረግ አለብህ?
3. ከሐሰት ትምህርትና ከአስተማሪዎች ጋር ሊኖርህ የሚገባ ግንኙነት ምን መሆን አለበት?
4. በመደጋገም ዮሐንስ ከሚጠቅሰው ያስተዋልከው ምንድን ነው?

## ጥናት ሰባት

## “መልካም ምስክርነት”

**3ዮሐ. 1፡1-15**

*መግቢያ፡-* በዛሬው ጥናት ዮሐንስ በተለያዩ ሰዎች ሕይወት የተሰማውን ደስታና ሀዘን ከገልጸበት መንገድ እውነትን ስለመያዝና እንግዶችን ስለመቀበል እናጠናለን።

*ዓላማ፡-* በእውነት መራመዳችን ለሌሎች ደስታና እረፍት እንደሚያመጣ ለማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁጥር 1-2 ዮሐንስ ጋይዮስን እንዴት ነው የሚገልጸው? ስለምንስ ነው የሚጸልይለት?
2. ከቁጥር 3-4
   - በጋይዮስ ዘንድ የነበረ ለዮሐንስ የደስታ ምክንያት የነበረው ምንድን ነው?
   - በነዚህ ቁጥሮች በመደጋገም የተጠቀሰው ሀሳብ ምንድን ነው?
3. ከቁጥር 5-8 እንግዶችን በተመለከተ ለጋይዮስ የተመሰከረለት ምንድን ነው?

   ለመሪው፡-
   - የታመነ/ጥሩ ሥራ ይሠራል
   - ፍቅርን ያሳያል
   - ለጌታ እንደሚያደርግ ያክል ለሌሎች ያደርጋል
   - በእውነት/ በቅን መንፈስ እንግዶችን ይቀበላል
4. ከቁጥር 9-10 የዲዮጥራጢስ ምግባርን በዝርዝር ተመልከቱ።

   ለመሪው፡-
   - ሐዋሪያውን አይቀበልም
   - ክፉ ቃልን ያስወራል (ያማል)
   - በጎ ለማድረግ የሚተጉን ልብ ያሻክራል
   - እንግዳ አይቀበልም
   - እንግዳ የሚቀበሉትን ያከላክክላል
5. በቁጥር 11-12 የሰጠው ምክርና ስለ ለድሜጥርስ የተናገረው ምንድን ነው?
6. በቁጥር 13-15 መልዕክቱን ያጠቃለለባቸው ሦስት ሀሳቦች ምን ምን ናቸው?

   ለመሪው፡-
   - ሊጽፈው ያለው ብዙ መሆኑ
   - ፊትለፊት ሊያቸው መናፈቁን
   - ከሌሎች ሰላምታን በማቅረብ

### ማዛመድ

1. ከጋስዮስና ከድሜጥሮስ ሕይወት የተማርከውን (ክርስቲያን ሁሉ ሊኖረው ስለሚገባው ባህርይ) ለቡድንህ አካፍል። ለምንስ አይነት እርምጃ ያነሳሳሃል?
2. መውደድ ማለት ጥፋትን ማለፍ ስላለመሆኑን ከዚህ ክፍል የተረዳህውን አካፍል።
3. የዲዮጥራጢስ ድርጊት ከ 1ዮሐ. 5፡2 ጋር መቃረኑን ልብ በል። ከእንደዚህ አይነት ሕይወት ለመራቅ ምን ማድረግ አለብህ? እንዴትስ በኑሮህ ትገልጸዋለህ?